የሰ/መ/ቁ. 132861

ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ እርጋጤ መድበው 2. ወ/ሮ አበበች ከተማ

3 አቶ ጋዲሳ ረጋሳ 4. አቶ መኮንን ገ/ማርያም

5 አቶ ኃይሌሚካኤል ሰናይ 6. አቶ ዘውዱ ገ/ጻድቅ

7. አቶ እንዳለ ጎሣዬ 8 . አቶ መኩሪያ ወ/ሥላሤ

9 አቶ አለምሰገድ ወ/አማኔኤል 10. የ፲ አለቃጥላሁን ከበደ

11 አቶ መስፍን በቀለ 12. አቶ አብርሃም ለማ

13. አቶ በረሁን ማሞ 14. አቶ ተምትሜ ዓለሙ

15 ም/መ/አለቃ አባተ መድበው 16. አቶ ደምሴ ንጉሴ

17. አቶ ሽመልስ ዓለሙ 18. አቶ ፍጹም ካህሳይ

19 አቶ ግርማ ተሰማ 20. አቶ አያሌው ፋንታዬ

21 አቶ ወንድሙ ገብሬ 22. አቶ ኃይሉ ቡራዩ

ተጠሪ፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ- ነ/ፈጅ ሄኖክ መሳይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የጉዳዩ አመጣጥ የዘለቄታ ጡረታ አበል እንዲከፈል እንዲወሰን ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አጀንሲ የዘለቄታ የጡረታ አበል እንዲወሰንላቸው ጥያቄ አቅርበው ኮሚቴው ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 27 እና በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63 ተራ ቁጥር 3 መሠረት አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የሚወሰንላቸው የአንድ ጊዜ የዳረጎት አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ወይም የዘለቄታ ጡረታ አበል የለም ሲል ወስኗል፡፡፡

ይህን ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኖቹ አመልካቾች ይግባኝ ለማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበው የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ኮሚቴ ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ውሳኔውን ለማስለወጥ ይግባኝ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካቾች የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች መስከረም 18 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 19 /2/ ላይ ማንኛውም መንግሥት ሠራተኛ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ ጡረታ ያገኛል ሲል በግልጽ ደንግጎ እያለ የአመልካቾች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ነው በማለት የዘለቄታ የጡረታ አበል አይገባቸውም ተብሎ መወሰኑ ግልጽ የሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው አቤቱታውን መርምሮ የአመልካቾች የጡረታ መብት ጥያቄ ከአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንጻር የአገልግሎት ዘመናቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዳረጎት አበልም ሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል ሊወሰንላቸው አይገባም ተብሎ በሥር የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል አዟል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በቀን 6//6/2009 ዓ.ም የተጻፈ መቃወሚያ እና መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን አመልካቾቹም መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ጉዳዩን አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካቾች በመንግሥት ሥራ እያገለገሉ ቆይተው ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በጽኑ እስራት ምክንያት አገልግሎት ያቋረጡ መሆናቸውን፣ የጽኑ እስራት ጊዜያቸውን ጨርሰው የወጡ መሆናቸውን፣ አስቀድመው በመንግሥት ሥራ ያገለገሉበት ዝቅተኛው 10 ዓመት ሲሆን ከፍተኛው 18 ዓመት መሆኑን አመልካቾች ያቀረቡት ዝርዝር እንዲሁም ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የሥር መንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አጀንሲ ኮሚቴ እንዲሁም የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት ዋናውና መሠረታዊው ነጥብ የአመልካቾች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል አይገባቸውም የሚል ነው፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሻሻለው የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5 /2/ አንጻር ሲታይ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን መመልከት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሠረቱ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረበው መልስ ላይ በአዋጅ ቁጥር 209/55፣በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 5/67 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ የተደነገገውን ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት እያነሳ የተከራከረ ሲሆን በእነዚህ አዋጆች ላይ የተደነገገው እና የአሁኑ ተጠሪዎች ስለመብታቸው የሚከራከሩበት የአገልግሎት ዘመን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 ተተክቷል፡፡ በተሻሻለው አዋጅቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ ላይ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 1/ በተደነገገው መሠረት የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልክ ይከፈለዋል ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር ዓመት ማገልገል ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 18/1/ መሠረት የጡረታ እድሜ መድረስ ነው፡፡ የአመልካቾች የጡረታ እድሜ ከ60 ዓመት በላይ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ ሲከራከር የነበረ አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ ጡረታ አበል አይገባቸውም በማለት ነው፡፡ ይህ ክርክር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19/2/ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ ደግሞ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ የተተካ በመሆኑ የተጠሪ የ20 ዓመት አገልግሎት ክርክር ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63/3/ ድንጋጌም ቢሆን አዋጁን ሊጻረር አይችልም፡፡

ምክንያቱም መመሪያው አዋጁን ማስፈጸሚያ ነው እንጂ በአዋጁ የተደነገገውን ድንጋጌን ሊቃረን የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ ምክንያት ነው፡፡

ሌላው የተጠሪ ክርክር የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ አዋጁ በሚወጣበት ጊዜ በሥራ ላይ ያሉትንና ከአዋጁ በኃላ የጡረታ እድሜያቸው ሲደርስ ጡረታ የሚወጡትን የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ክርክር የማሻሻያ አዋጁን አንቀጽ 5/2/ 'ን' መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ የአሁኑ አመልካቾች የዘለቄታ የጡረታ አበል እየጠየቁ ያሉት በገዛ ፈቃዳቸው ሥራ ለቀው ሳይሆን ታስረው በመቆየታቸውና እድሜያቸው ለጡረታ የደረሰ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 11/9/ አንጻር ሲታይ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊና ህጋዊ ሁኔታዎችን በአግባቡ ሳያጤኑ የሰጡት ውሳኔም ሆነ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ኮሚቴ በቀን 9/6/2008 ዓ/ም ፣ የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በቁጥር ይ/1/1/154/2008 በቀን 28/7/2008 የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 126747 ሰኔ 14 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የጡረታ አበል ክፍያ የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከፀናበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካቾች እንዲከፍላቸው ተወስኗል፡፡
3. የዚህ ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይድረሳቸው፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡